የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7th Year No. 26
ADDIS ABABA - 31st May, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፰/፲፱፻፺፫ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ግብርና ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ
አዋጅ ........................................... ገጽ ፩ሺ፭፻፲፩

## CONTENTS

Proclamation No. 238/2001
Ethiopian Agricultural Sample Enumeration
Commission Establishment
Proclamation ........................................... Page 1511

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፰/፲፱፻፺፫
## የኢትዮጵያ ግብርና ቆጠራ ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚተዳደር በመሆኑና ይህንኑ የተመለከተ መሠረታዊ የግብርና መረጃ በማስፈለጉ፤

ዝርዝር የሆኑ የግብርና መረጃዎች መኖር በአገር አቀፍና በክልሎች፣ ከዚያም በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ለሚቀየሱ ፖሊሲዎችና የልማት ፕሮግራሞች አፈጻጸም፣ ክትትልና ቁጥጥር አስተማማኝ መሠረት በመሆኑ፤

ይህንኑ የቆጠራ ሥራ በተቀላጠፈና በአስተማማኝ ሁኔታ ለመምራት በአገር አቀፍ፣ በክልሎችና ከዚያም በታች ባሉ የአስተ ዳደር እርከኖች ደረጃ በበላይነት የሚመራና የሚያስተባብር እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ያለው ኮሚሽን ማቋቋም በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ግብርና ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፴፰/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO.238/2001
## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN AGRICULTURAL SAMPLE ENUMERATION COMMISSION

WHEREAS, the majority of the Ethiopian population is engaged in Agriculture, and it is necessary to have basic statistical information regarding this sector of the economy;

WHEREAS, the availability of detailed information regarding the agricultural sector is essential for policy and development programme formulations, monitoring and evaluation at national, regional and at lower administrative levels in a region;

WHEREAS, in order to manage the agricultural census operations efficiently and effectively, it is found necessary to establish a commission that have a life span of upto five years, and responsible for the overall management and coordination of agricultural census activities at national, regional and at lower administrative levels in a region;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Agricultural Sample Enumeration Commission Establishment Proclamation No.238/2001".

፪· <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "የግብርና ቆጠራ" ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ ወይም በተወሰነ ብሔራዊ ክልል በተለይም ስለእርሻ መሬት ይዞታና የሰብል ምርት መጠን፣ ስለቤት እንስሳትና ንብ፣ በግብርና ሥራ ስለተሰማራው የሰው ኃይል፣ ስለግብርና መሣሪያዎች ይዞታና አጠቃቀም፣ ስለ መስኖ ሥራ፣ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረ–ተባይና ሌሎች ተመሳሳይ መረጃዎችን አጠቃቀም በተመለከተ ወካይነት ባለው ከፍተኛ የናሙና መጠን በመጠቀም መሠረታዊ መረጃ ዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመገምገም፣ የመተን ተንና ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች የማሠራጨት ተግባር ነው።

፪· "ባለሥልጣን" ማለት የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥ ልጣን ነው፤

፫· "ኮሚሽን" ማለት የግብርና ናሙና ቆጠራውን ሥራ በበላይነት እንዲመራና እንዲያስተባብር በማዕከል፣ በክልል፣ በዞንና በወረዳ የሚቋቋመው ኮሚሽን ነው፤

፬· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተጠቀሰው ማንኛውም ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ መስተዳድርንም ይጨምራል፤

፭· "የመንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ማናቸውም የሚኒ ስቴር፣ የኮሚሽን፣ የባለሥልጣን፣ የጽሕፈት ቤት፣ ተቋም ወይም ማናቸውም ሌላ የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤

፮· "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው።

፫· <u>ስለመቋቋም</u>

፩· የኢትዮጵያ ግብርና ቆጠራ ኮሚሽን /ከዚህ በኋላ "ኮሚሽን" ተብሎ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

፪· ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ይሆናል።

፫· የሚኒስትሮች ምክር ቤት የቆጠራውን ሥራ ለማስፈጸም ደንብ የማውጣት ሥልጣን ይኖረዋል።

፬· <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

፩· ኮሚሽኑ፤
   ሀ) ማዕከላዊ ኮሚሽን፤
   ለ) የብሔራዊ ክልል ኮሚሽን፤
   ሐ) የዞን ኮሚሽን፤
   መ) የወረዳ ኮሚሽን ፤ እና
   ሠ) እንደ አስፈላጊነቱ የቀበሌ ኮሚቴዎች ፤
   ይኖሩታል።

፪· ባለሥልጣኑ የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።

፭· <u>የማዕከላዊ ኮሚሽኑ አባላት</u>

ማዕከላዊ ኮሚሽኑ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩· ጠቅላይ ሚኒስትር/ተወካይ ...................... ሰብሳቢ
፪· የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ሚኒስትር ............................... አባልና ም/ሰብሳቢ
፫· የግብርና ሚኒስትር .....................................አባል
፬· የማስታወቂያና ባሕል ሚኒስትር ......................... "
፭· የገንዘብ ሚኒስትር ...................................... "
፮· የግብርና ምርምር ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ....... "

2. *Definitions*

In this Proclamation unless the context requires otherwise :

1) 'Agricultural Census'' means the collection, compilation, evaluation, and dissemination of statistical data especially regarding agricultural holdings and volume of crop production, livestock and beehives, manpower engaged in agricultural activities, the use and holding of agricultural machinery, irrigation, improved seeds, fertilizer, pesticide and othe similar statistical information at the national and regional levels based on representative large scale sample;
2) "Authority" means the Central Statistical Authority;
3) "Commission" means a body established to lead and coordinate the tasks of Agricultural Census at national, regional, zonal and wereda levels;
4) "Region" means any region referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes, for purposes of the implementation of this Proclamation, the Administration of Addis Ababa and Dire Dawa;
5) "Government Office" means any Ministry, Commission, Authority, Office, Institution, Bureaux or any other Central or Regional government office; and
6) "Person" means any natural or juridical person.

3. *Establishment*

1) The Ethiopian Agricultural Sample Enumeration Commission (hereinafter referred to as the "Commission") is hereby established.
2) The Commission shall be accountable to the Council of Ministers.
3) In order to execute the agricultural census activities the Council shall have the power to issue census order.

4. *Organization of the Commission*

1) The Commission shall have:
   (a) a Central Commission;
   (b) National or Regional Commission;
   (c) Zonal Commission;
   (d) Wereda Commission; and
   (e) Kebele Committees as may be necessary.
2) The Authority shall serve as the Secretariat of the Commission.

5. *Members of the Central Commission*

The Central Commission shall have the following members:

1) The Prime Minister/Representative.....Chairperson
2) The Minister of Economic Development and Cooperation ...........Member and Vice Chairperson
3) The Minister of Agriculture ......................Member
4) The Minister of Culture and Information ........"
5) The Minister of Finance ............................... "
6) The Director General of Agricultural Research Organization ............................................... "

፯· የትምህርት ሚኒስትር ................................ ”
፰· የውሀ ሀብት ሚኒስትር ............................... ”
፱· የተፈጥሮ ሀብትና የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ .................................. ”
፲· የእንስሳትና የእንስሳት ተዋጽኦ ገበያ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ ..................................አባል
፲፩· የቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ሥራ አሥኪያጅ . ”
፲፪· በጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የክልል ጉዳይ ............ ዘርፍ ኃላፊ ............................................... ”
፲፫· የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ....አባልና ፀሐፊ።

፮· <u>የማዕከላዊ ኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ማዕከላዊ ኮሚሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

፩· የኢትዮጵያ ግብርና ቆጠራን በሚመለከት የፖሊሲ መመሪያ ማውጣትና አፈጻጸማቸውን መከታተል፤
፪· ቆጠራ የሚከናወንበትን ጊዜና የሚሰበሰበውን የመረጃ ዓይነት መወሰን፤
፫· ስለግብርና ቆጠራ ተግባር ለሕዝብ ማሳወቅ፤ እና
፬· ከብሔራዊ ክልል ኮሚሽን በሚቀርቡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ መስጠት።

፯· <u>የብሔራዊ ክልል ኮሚሽን አባላት</u>

የብሔራዊ ክልል ኮሚሽኑ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

፩· የክልሉ መንግሥት ፕሬዚዳንት .. .. ሰብሳቢ
፪· የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ........................................ አባልና ም/ሰብሳቢ
፫· የግብርና ቢሮ ኃላፊ ..................... አባል
፬· የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ .................. ”
፭· የማስታወቂያ ቢሮ ኃላፊ ............. ”
፮· የትምህርት ቢሮ ኃላፊ.................. ”
፯· የኢንቨስትመንት ጽ/ቤት ኃላፊ ..... ”
፰· የፖሊስ ኮሚሽነር ........... ”
፱· የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ቢሮ/ጽ/ቤት ኃላፊ ”
፲· በክልሉ በግብርና እንቅስቃሴ ላይ የተሠማሩ ሌሎች ድርጅቶች ኃላፊ...................... ”
፲፩· የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ .................. አባልና ፀሐፊ።

፰· <u>በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ ኮሚሽኖች አባላት</u>

፩· በዞንና በወረዳ የሚቋቋሙት ኮሚሽኖች አባላት ከክልል ኮሚሽኑ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።
፪· የዞንና የወረዳ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዎች ሊቃነመናብርት እንደአግባቡ በዞንና በወረዳ ደረጃ ለሚቋቋሙ ኮሚሽኖች ሰብሳቢዎች ይሆናሉ።
፫· በየደረጃው የሚገኝ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ኃላፊ ወይም ተጠሪ እንደአግባቡ በዞንና በወረዳ ለሚቋቋመው ኮሚሽን ፀሐፊ ይሆናል።

፱· <u>በብሔራዊ ክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ ኮሚሽኖች ሥልጣንና ተግባር</u>

፩· በብሔራዊ ክልል፣ በዞንና በወረዳ የሚቋቋመው ኮሚሽን ተጠሪነቱ በደረጃ ቀጥሎ ለሚገኘው የበላይ ኮሚሽን ሆኖ በየደረጃው የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፣



7) The Minister of Education ..................... Member
8) The Minister of Water Resources ................ ''
9) General Manager of Natural Resources and Environmental Protection Authority....... ''
10) General Manager of Animal, Animal Products and By-Products Marketing Development Authority ............................... ''
11) The General Manager of Coffee and Tea authority ................................................ ''
12) The Head of the National/Regional Affairs Sector in the Prime Minister Office ............. ''
13) The General Manager of the Authority ........................ Member and Secretary.

6. *Powers and Duties of the Central Commission*

The Central Commission shall have the following powers and duties:

1) to initiate policy directives regarding the Ethiopian Agricultural Sample Enumeration and follow up the implementation of same;
2) to determine the time for carrying out the agricultural Census as well as the type of information to be collected;
3) to notify the public on the agricultural census activities; and
4) to give decisions on matters submitted by National Regional Commissions.

7. *Members of the National Regional State Commission*

The Commission shall have the following members:

1) President of the National/Regional StateChairperson
2) Head of Planning and Economic ... Development Bureau ......................Member and vice Chairperson
3) Head of Agricultural Bureau .......................Member
4) Head of Finance Bureau.................................. ''
5) Head of Information Bureau .............................''
6) Head of Education Bureau ............................... ''
7) Head of Investment Office ................................''
8) Police Commissioner........................................ ''
9) Head of Disaster Prevention and Preparedness Bureau/ Office ....................................................... ''
10) Head of Other Organizations which have affiliation with agricultural activities...............................''
11) Head of Branch Statistical Office of the Authority .....................Member and Secretary.

8. *Members of the Zonal and Wereda Commission*

1) Members of the zonal and Wereda Commissions shall be determined by directives to be issued by the National/Regional State Commissions.
2) The Chairpersons of the executive committees of Zonal and Wereda Administrations shall be the chairpersons of the respective Agricultural Sample Enumeration Commissions.
3) the head of the Authority or his representative in each Administrative hierarchy shall serve as a member and secretary to the respective commission.

9. *Powers and duties of the National/Regional, Zonal and Wereda Commissions.*

1) Commissions established at the National/Regional, Zonal and Wereda levels each being accountable to the next higher Commission, shall have the following powers and duties within their respective jurisdiction;

ሀ) ከደረጃው ቀጥሎ ከሚገኘው የበላይ ኮሚሽን የሚተላለፉ መመሪያዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ፣

ለ) ለግብርና ቆጠራው አፈጻጸም በየአስተዳደር እርከኑ ውስጥ የሚገኘውን ሕዝብ እንደዚሁም መ/ቤቶችና ድርጅቶች የመቀስቀስና የማስተባበር፣

ሐ) በየአስተዳደር እርከኑ ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ ለቆጠራው አፈጻጸም ስልቶችን የመቀየስ፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን መፍታትና ለቆጠራው ሥራ ስኬታማነት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

መ) ከደረጃ ቀጥሎ ከሚገኘው የበላይ ኮሚሽን የሚሰጡ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን።

፪· በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋመው ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል።

፲· የስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

፩· በየደረጃው የሚቋቋመው ኮሚሽን በሰብሳቢው ጥያቄ ወይም ከግማሽ በላይ የሆኑ የኮሚሽን አባላት ሲጠይቁ ይሰበሰባል።

፪· ከኮሚሽኑ አባላት አብዛኛዎቹ ሲገኙ ምልዐተ ጉባዔ ይሆናል።

፫· የኮሚሽኑ ውሳኔ በድምፅ ብልጫ ይሆናል። ድምፁ እኩል ለእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፬· ኮሚሽኑ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል።

፲፩· የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር

ባለሥልጣኑ በማቋቋሚያ ሕግ ከተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት በተጨማሪ የግብርና ቆጠራው አስፈጻሚ ድርጅት ነው ። ይህ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሥልጣኑ የግብርና ቆጠራውን ለማከናወን የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

፩· ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለግብርና ቆጠራው ሥራ የሚያስፈልጉ መጠይቆች፣ መመሪያዎችና የመስክ መገልገያ ዕቃዎች የማዘጋጀት፣

፪· የግብርና ቆጠራውን የሚመለከቱ መረጃዎች የመሰብሰብ፣ ለዚህም አግባብ ያላቸው ሠነዶችና መዛግብት የመመርመርና ምርመራውንም ለማከናወን አግባብ ባለው ጊዜ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ወደ ማንኛውም ሰው ቅጥር ግቢ ወይንም ይዞታ የመግባት፣

፫· በግብርና ቆጠራ የተሰበሰበውን መረጃ ማደራጀት፣ መተንተንና ሪፖርቱን አዘጋጅቶ ለማዕከላዊ ኮሚሽኑ የማቅረብና ሲፈቀድም የማሠራጨት፣

፬· በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፩(፪) መሠረት ቆጠራው እንዲካሄድ በተወሰነበት ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ካለው አካል ጋር በመመካከር በማንኛውም የመንግሥት መ/ቤት ሠራተኞች፣ ንብረትና አገልግሎት ትብብር በመጠየቅ የመጠቀም፣

፭· የግብርና ቆጠራውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ አግባብ

(a) to ensure the implementation of directives issued by the next higher commission;

(b) to mobilize the public, government offices, and organizations for the execution of the Agricultural Sample Enumeration activities at different Administrative levels;

(c) to device ways and means as well as find solutions to the problems encountered based on prevailing objective conditions of the particular Administrative hierarchy, for the execution of the Agricultural Sample Enumeration activities; and

(d) to perform other duties assigned to it by the next higher commission.

2) The powers and duties of Committees to be established at kebele level shall be determined by directives issued by the Commission.

10. *Rules and Procedures of the Commissions*

1) The Commissions established at each level shall meet at the request of the Chairperson, or where more than half of the members so require.

2) There shall be a quorum where the majority of the members of the Commission are present.

3) Decisions of a Commission shall be made by a majority votes; in case of a tie, the Chairperson shall have a casting vote.

4) Each Commission shall draw up its own rules and procedure.

11. *Powers and Duties of the Authority*

In addition to the powers and responsibilities given to it by law, the Authroity shall be responsible for the execution of the Agricultural Sample Enumuration. Without limiting the generality of the foregoing, the Authority shall, in order to carry out the Agricultural Sample Enumeration, have the following powers and duties:

1) to in collaboration with concerned bodies, prepare, questionnaires, manuals and logistics necessary for undertaking the Agricultural sample Enumeration;

2) to collect statistical data relating to Agriculture and to that end, to inspect relevant documents and records as well as enter private premises or holdings at appropriate time as the rules and regulations of the government permit;

3) to compile and analyze Agricultural Sample Enumeration data collected, and submit the report to the Central Commission, and disseminate same upon approval;

4) to utilize the personnel, property and services of any government office at the time set in accordance with article 11(2) given here in above in consultation with the relevant organs, and when it finds it necessary, for carrying out the the Agricultural Sample Enumeration activities; and

